# ኮሜርስ ክበቤ

ጽሑፍ አቅራቢ፣ እንኮሳ አያና

መዝናኛ በታዬ ኮሜርስ ክበቤ
ስምሽን እየጠራሁ አርማሽን አንግቤ
የጥንት የጠዋቱን ካባሽን ደርቤ
ጊቢሽን ስረግጠው ይደሰታል ልቤ
ሞራሌ ከፍ ይላል ይረጋል ሃሣቤ
ቅዳሜ ማለዳ ጧት ተነስቼ
ልብሴን ለዋውጬ ኳስ ሜዳ ገብቼ
እርካታ አገኛለሁ ቴኒስ ተጫውቼ
ከእርካታውም በላይ ቴኒስ መጫወቱ
ለአካል ጥንካሬ ይጠቅማል ስፖርቱ
ደግሞ ይቀጥላል እሁድ በጠዋቱ
ሳምንቱን ወራቱን አይቆምም ኡደቱ
ኮሜርስ ክበቤ ካልሄድኩኝ ቅዳሜ
ውል ትለኛለች ትመጣለች በ'ልሜ
እሁድ በማለዳ ካልሄድኩኝ ደግሜ
ያቅበጠብጠኛል ይነሳል ሕመሜ
ከሰኞ እስከ አርብ ከሰዓት በኋላ
እንጫወታለን ሄደን ከረንቦላ
ሻይ ቡና እየጠጣን እየበላን ቆሎ
ጨዋታው ሲመስጥ ልብን አንጠልጥሎ
ተጫዋች ሲጫወት ሕጉን ተከትሎ
የቀናው አሸናፊ ይፎክራል ዘሎ
ጭብጨባው ይቀልጣል ድሉን ተቀብሎ
እንዲያ እንዲያ እያለ ይሄዳል ሰዓቱ
መንዝ ይጀምራል ሁሉም ወደ ቤቱ
ኮሜርስ ክበቤ መዝናኛ በታዬ
እድሬም አንቺው ነሽ የኔ ዋስትናዬ
እስቲ እናስታውሳቸው አባላት በሙሉ
አገር ውስጥ ያለን ውጭ ያሉትም ሁሉ
መሥራች አባላትን ይባርካችሁ በሉ

የሞቱትም ይሁን በሕይወትም ያሉ
ስማቸው ይጠራ ይዘከር ይከበር በዓሉ
ከስድሳ ዓመት በፊት መሥራች የነበሩ
በሕይወት የተገኙት ይውጡ ይናገሩ
ለኛ ይጠቅመናል ከነርሱ መማሩ
ከዚህች ዕለት በፊት ሞት የቀደማቸው
ነፍሳቸውን ይማር አፈር ይቅለላቸው
በአጋጣሚ ሁሉ ይነበብ ገድላቸው
በታሪካዊነት ይታወስ ሥራቸው
ለቋሚው ይጠቅማል አርአያነታቸው
እህት ወንድሞቼ እስቡ በእርጋታ
የእነዚህ ሰማዕታት አለብን ውለታ
የክበቡ ዓላማ ግቡን እንዲመታ
መደገፍ አለብን ክበቡን በጋራ
በሚያስፈልግ ሁሉ ተባብረን እንስራ
እንቶ ፈንቶ ትተን ቁም ነገር እናውራ
የክበቡ ዓላማ በተግባር ይተርጎም
ማንበቢያ ይዘጋጅ ላይብረሪ ይቋቋም
ክበቡ ይታወቅ በቀዳሚነቱ
በዓሉ ይከበር ስድሳ አምስት አመቱ
ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ ይነገር ታሪኩ
ጥንት እንደነበረ ሳይቀየር መልኩ
ከሙያ ማህበራት መሆኑ አንጋፋ
ሁሉም እንዲረዳው ይነገር በይፋ
ነጋሪት ይጎሰም መለከት ይነፋ
ዓላማው ይተግበር የጥንት የጠዋቱ
ወደ አመራር ይምጣ ይሳተፍ ወጣቱ
አዲስ ሃሳብ ይፍለቅ ይመዝገብ እመርታ
ወደ ፊት እንገስግስ ፍፁም እናመንታ
ዕድገቱ ይመጣል የማታ የማታ

እቅዱ ይተግበር ሁሉም በጊዜያቱ
ሥራው አይጓተት በየምክንያቱ
ሁሉም ይተባበር ይፋጠን ልማቱ
መዝናኛው ይዘጋጅ ሁሉን የሚያረካ
አካል የሚያዳብር ሞራል የማይነካ
የሚሳተፉበት ወጣት አዛውንቱ
ፆታ ሳይገድበው ወንዱም ሆነ ሴቱ
ተራውን ጠብቆ ልክ በሰዓቱ
ሕጉንም አክብሮ ሳይጣስ ስርዓቱ
ክበቤ እንድትገኝ ይህንን አሟልታ
ፍጹም ምኞቴ ነው ለማየት አንዳፍታ
በዚህ ከተስማማን አባላት በሙሉ
የተዛቡ ሁሉ ይስተካከላሉ።